# በኦስትሪያ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ !!!

## አስደሳች ዜና



ለሁለት ዓመታት ያህል በእስር ሲማቅቁ ከቆዩ በኋላ በቅርቡ ከተፈቱት የቅንጂት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ፓርቲ ከፍተኛ አመራር መካከል አምስቱ በተለያዩ የአውሮፓ አገሮች የስራ ጉብኝት በማድረግና ከኢትዮጵያውያንም ጋር በመገናኘት ስለ አገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ውይይቶችን በማድረግ ላይ ይገኛሉ ።

እኛም በኦስትሪያ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ይህ ዕድል እንዳያመልጠን ያደረግነው ጥረት ተሳክቶልን እነሆ **በ Oct.02 2007 ከሰዓት በኋላ 17.00 ሰዓት ላይ ቪየና አውሮፕላን ማረፊያ ይደርሳሉ** ። በዕለቱም በአውሮፕላን ጣቢያ በመገኘት ደማቅ አቀባበል እንዲያደርጉላቸው በትህትህና እንጠይቃለን

የልዑካን ቡድኑ ኢትዮጵያውያንን በማግኘት እስር ቤት በነበሩበት ወቅት ላደረጉላቸው ሁለገብ ርዳታ ምስጋናቸውን ለማቅረብና ስለ አገራችን ወቅታዊ ፖለቲካ ግልፅ የሆነ ውይይት ለማድረግ ፍላጎታቸው በመሆኑ **Oct.03.2007 ከ 17.30 ሰአት ጀምሮ Afro Asia Institute, Türkenstr. 3, 1090 Wien** በሚገኘው አዳራሽ ስብሰባ ይደረጋል።

በመሆኑም ይህን ዳግም የማይገኝ አጋጣሚ በመጠቀም በአገራችን የፖለቲካ ዙሪያ የበለጠ ይረዱ ዘንድ በትህትና ተጋብዘዋል። ስብሰባው ነጻና ግልፅ በመሆኑ ቅሬታዎን ወይም አስተያየትዎን ያለ ምንም መታቀብ ማቅረብ እንደሚችሉ አበክረን ልናስገነዝብ እንወዳለን ።

**የልዑካን ቡድኑ ስም ዝርዝር ፤**

አቶ ሙሉነህ ኤዮኤል የቅንጂት ዋና ጸሃፊ

ዶ/ር ያቆብ ሃይለማሪያም

አቶ አባይነህ ብርሃኑ

አቶ ክፍሌ ጥግነህ

አቶ አስቻለው ከተማ

አስተባባሪ ኮሚቴው !